# አምልኮ

worship የሚለውን የእንግሊዝኛውን ቃል አማርኛው

-ስግደት ወይም መስገድ

-ከፍተኛ ክብር መስጠት

-አምልኮ ይለዋል

worshipን የ እንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት

- to honor a divine being
- to show reverence for divine being

የ ግሪኩ ትርጉም worship የሚለውን ብዙ ግዜ "proskuneo" ብሎ ይተረጉመዋል ።

pros ማለት  toward ሲሆን

kuneo ማለት to kiss the hand , knee, leg

በዚህ መሰረት proskuneo ማለት አጎንብሶ እጅ መሳም፥ ጉልበት መሳም ከፍ ሲልም እግር መሳም ሊሆን ይችላል።

proskuneo ፡- obeisance የሚለውንም ትርጉም ይሰጠናል ይህም አንገትን ዝቅ አድርግ መስገድ እንደማለት ነው ።

proskuneo፡- prostrate የሚለውንም ትርጉም ይሰጠናል ይህም ፊትን ደፍቶ ለጥ ብሎ መተኛት እንደማለት ነው።

ባጠቃላይ proskuneo የሚለው ቃል ለአንድ አካል መገዛትን፥ መታዘዝን ያመለክታል።

የ ህብሩ(Hebrew) ትርጉም worship የሚለውን ቃል በ አብዛኛው ጊዜ "shachah" ብሎ ይተረጉመዋል ።

shachah - bow down - መንበርከክ

- fall down - መውደቅ
- obeisance - አንገትን ዝቅ ማድረግ መስገድ
- prostrate - ፊትን ደፍቶ ለጥ ብሎ መትኛት

ባጠቃላይ worship የሚለው ሀሳብ የግሪኩም ሆነ የ ህብሩ ቃል የሚያመለክቱት ለ እግዚአብሔር ከልብ የሆነ መታዘዝ ወይም መገዛት ነው።

# በብሉይ ኪዳን አምልኮ እንዴት ተብራራ

በብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ "shachah"  ወይም worship የሚለው ቃል የ ተጠቀሰው ዘፍጥረት 22-5  ላይ ነው።

ዘፍጥረት 22 (አዲሱ መ.ት)

---

1 ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አብርሃምን ፈተነው፤ “አብርሃም!” አለው። እርሱም “አቤቱ አለሁ” አለ።

2 እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ “የምትወደውን አንዱን ልጅህን፣ ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ምድር ሂድ፤ እኔ በማመለክትህ በአንዱ ተራራ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው” አለው።

3 በማግስቱ ጠዋት አብርሃም ማልዶ ተነሣ፤ አህያውን ጭኖ፣ ሁለት አገልጋዮቹንና ልጁን ይስሐቅን ይዞ፣ ለመሥዋዕት የሚበቃውን ዕንጨት ከቈረጠ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወዳመለከተው ቦታ ለመሄድ ጒዞውን ጀመረ፤

4 በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ቦታውን ከሩቅ ተመለከተ፤

5 አገልጋዮቹንም “እናንተ አህያውን ይዛችሁ እዚህ ቈዩን፤ እኔና ልጁ ግን ወደዚያ ሄደን ለእግዚአብሔር ሰግደን እንመለሳለን” አላቸው።

በዚህ ክፍል ቁጥር 5 ላይ አብርሃም እኔና ልጄ ግን ወደዚያ ሄደን ለእግዚአብሔር ሰግደን እንመለሳለን በማለት እግዚአብሔር እንዳመለከ እናያለን። አብርሃም እግዚአብሔርን ያመለከው ለእግዚአብሔር ሀሳብና ፈቃድ በመታዘዙ ና በ መገዛቱ ነው።

ሌሎችም  የብሉይ ኪዳን ክፍሎች

መዝሙር 95-6

መዝሙር 5-7

# በአዲስ ኪዳን አምልኮ እንዴት ተብራራ

proskuneo የሚለው ቃል ወደ 59 ግዜ ተጠቅሳል።

ማቴዎስ 2:1-2

ማቴዎስ 2-11

ማቴዎስ 8-2

ማቴዎስ 9-18

ማቴዎስ 20-20

ማቴዎስ 28-9

ማቴዎስ 28:17

## መዝጊያ

በ ዩሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4:21-24 እየሱስ ክርስቶስ ከ ሳምራዊቷ ሴት ጋር በነበረው ንግግር ስለ አምልኮ እጠቃላይ በሆነ መልኩ መመሪያ ነው። በዚህ ክፍል እየሱስ ክርስቶስ አምልኮ እንዴት እንደሚደረግ፥ ስለ አምልኮ ቦታ ና ስለ አምልኮ ምንነት አስተምራል።

ዮሐንስ 4 (አዲሱ መ.ት)

———

21 ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ “አንቺ ሴት፤ በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ።

22 እናንተ ሳምራውያን ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን ድነት ከአይሁድ ስለ ሆነ ለምናውቀው እንሰግዳለን።

23 በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤ አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል።

24 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል።”

ቁጥር 21-22 ክርስቶስ አምልኮ የቦታ ጉዳይ እንዳልሆነ ይልቁንም በየትኛውም ቦታ ብንሆን እግዚአብሔር ከልብ ከሆነ መታዘዝና መግዛት ማምለክ እንዳለብን።

ቁጥር 23-24 እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነ የምናመልከውም በመንፈስና በእውነት መሆን እንዳለበት።

በመንፈስ ሲል እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ከልብ ከሆነ ለ እግዚአብሔር መታዘዝና መግዛት ማለት እንደሆነ።

በእውነት ሲል አምልኮ መሆን ያለበት በ እግዚአብሔር ቃል መሰረት ና ክርስቶስን ማዕከል ባደረገ መልኩ መሆን እንዳለበት።